# በአማራ ክልል ማዕከላዊ ጎንደር ግጭት ተቀስቅሷል

By wazemaradio

SEP 30, 2019

> *በአማራ ክልል ማዕከላዊ ጎንደር በፀጥታ ሀይሎችና በታጣቂ ሀይሎች መካከል በተቀሰቀሰ ግጭት የሰው ህይወት መጥፋቱን ከአካባቢው የሚወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።*



ዋዜማ ራዲዮ- በማዕከላዊ ጎንደር ጭልጋ ወረዳ፡ ከአይከል ከተማ አንሥቶ እስከ ጓንግ- ቡሆና ድረስ በአካባቢው ታጣቂ ገበሬዎች (የቅማንት) እና በክልሉ ልዩ ኃይል መካከል በመስከረም 16/2012 ዓ.ም ጀምሮ የተቀሰቀሰው ግጭት እስከዛሬ ጧት ድረስ እንዳልተረጋጋ በአካባቢው ያነጋገርናቸው እማኞች ገለጹ።

ግጭቱ ከተቀሰቀሰ ዛሬ 4ኛ ቀኑ ሲሆን ከአይከል ከተማ ልዩ ስሙ ጓንግ አንስቶ እስከ ቡሆና አካባቢ አልፎ አልፎ የተኩስ ድምፅ እንደሚሰማ የዓይን እማኞች ገልጸዋል። በ16/01/2012 ዓ.ም የክልሉ ልዩ ኃይል ወደ አይከል ከተማ ሊገባ ሲል በታጠቁ የአካባቢው ገበሬዎች በልዩ ኃይሉ ላይ ተኩስ እንደከፈቱ እና ልዩ ኃይሉም የአጸፋ መልስ የተኩስ ልውውጥ በማድረጉ ግጭቱ ሊቀሰቀስ እንደቻለ ምንጮች ጠቁመዋል።

በግጭቱ እስካሁን ቁጥራቸው ያልታወቀ ገበሬዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።

በ2008ዓ.ም የክልሉ መንግሥት በማእከላዊ ጎንደር ዞን በቅማንት የማንነት ጉዳይ ላይ በተደረገው የወሰን ማካለል ሂደት ነጻ ቀጠና ሆነው እንዲቀጥሉ በተወሰኑት ጀጀቢት፣ ሸንፋና ልንጫ ሦስት ቀበሌዎች በመንግስትና በአካባቢው ገበሬዎች መካከል ከፍተኛ ያለመግባባት ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። በእነዚህ ሦስት ቀበሌዎች ከቅማንት በተጨማሪ የአማራ ተወላጆች በቀበሌዎች አብረው ይኖራሉ ።

የአማራ ክልል የሠላምና ደኅነነት ግንባታ ቢሮ ሓላፊ አቶ አገኘሁ ተሻገር 18/01/2012 ዓ.ም በሰጡት ማብራሪያ በማእከላዊ ጎንደር ጨልጋና አካባቢው የተፈጠረው የሰላም መደፍረስ፣ መንግሥት የማንነትና የአስተዳደር ጥያቄዎችን ለመፍታት እየሠራ ባለበት ወቅት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

## CATEGORIES

About Wazema
Art and Culture
Benegerachin Lay-Discussion
Book Review
Current Affairs
Fake News alert
Home
Letter From Addis
News
PODCASTS
Talking points
Uncategorized
Video
Wazema Dossier
Wazema Forum

## WAZEMA MEDIA

Wazema Media is legally registered organization founded in 2014 by Ethiopian exiled journalists, currently based in Addis Ababa, Ethiopia.

